በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የትምህርት ሚኒስቴር
ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Education
Debre Markos University

# የወጣ የጫራታ ማስታወቂያ

## ደ/ማ/ዩ/ብግጨ/34/2015 ዓ/ም

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ከመንግስት በተፈቀደለት በጀት **በሎት .1.*የስፖርት ትጥቅ በሎት .2. አንሶላ ግዥ*** ለመፈፀም በብሄራዊ ግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል ፡፡

*ስለሆነም በጨረታው መሳተፍ የሚችሉ ከዚህ በታች ማለትም፤*

1. በዘመኑ እና በዘርፉ የታደሰ የንግድ ስራ ፈቃድ እና የግብር ከፋይነት የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችል እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢነት ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፤
2. ለጨረታ ማስከበሪያ የሚሆን ማለትም **ለሎት.1.ስፖርት ትጥቅ** *ብር 60,000.00 ( ስድሳ ሽህ ብር) ለአንሶላ 100,000.00 (አንድ መቶ ሽህ ብር)* በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ ወይንም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ስም አሰርቶ ማቅረብ የሚችል
3. ዩኒቨርሲቲው **የአንሶላ ናሙና** የሚያቀርብ ሲሆን አሸናፊው ድርጅት በቀረበው ናሙና መሰረት ወይንም ተመሳሳይ የሆነ የጥራት ደረጃ ያለውን ማቅረብ የሚችል፤
4. ከላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተጫራቾች ሁሉ የጨረታ ዶክመንቱን ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አስተዳደር ህንፃ ቁጥር 27 ቢሮ ቁጥር 10 ወይንም አዲስ አበባ 4 ኪሎ ከቅድስት ማሪያም ቤ/ክርስቲያን ወረድ ብሎ **ሮሚና ካፌ ላይ 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 7** ከሚገኘው ቢሮአችን ማስታወቂያው በአዲስ ዘመን ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ15 ተከታታይ ቀናት **ለእያንዳንዱ ሎት** የማይመለስ **ብር 300.00/ ብር ሶስት መቶ/** በመክፈል መግዛት ይችላሉ፡፡
5. ጨረታው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በተከታታይ 15 ቀን አየር ላይ ቆይቶ በ16 ኛው ቀን ከጠዋቱ **4:00 ሰዓት ላይ ታሽጎ በዚያው እለት ከጠዋቱ 4:30 ተጫራቾች ወይንም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት** ይከፈታል፡፡
6. የጨረታውን ፋይናንሻል ዶክመንት እንዲሁም የጨረታ ማስከበሪያውን ለየብቻ አስተማማኝ በሆነ ማጣበቂያ በታሸገ ፖስታ በማድረግና በእያንዳንዱ ፖስታ ላይ የመ/ቤቱን ሙሉ ስምና አድራሻ በመፃፍ ማህተም በማድረግ በተጠቃለለ አንድ ፖስታ በማሸግ ማቀረብ ይኖርባቸዋል፡፡
7. ተወዳዳሪዎች የጨረታ ሰነዱን በአግባቡ በመሙላትና በማሸግ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ህንፃ ቁጥር 27 ቢሮ ቁጥር 10 ድረስ በመቅረብ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ከተከታታይ 15 ቀናት በኂላ በ16 ኛው ቀን **ከጠዋቱ 3:59** ድረስ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ሲኖርባቸው ጨረታው በዚሁ እለት **ከጠዋቱ 4:00** ሰዓት ላይ ተዘግቶ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት 4:30 ላይ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ህንፃ ቁጥር 27 ቢሮ ቁጥር 10 ውስጥ ይከፈታል፡፡ሆኖም ተጫራቾች በጨረታው ላይ መገኘት ካልቻሉ መስፈርቱን እስካሟሉ ድረስ በጨረታው ላይ ያልተገኙ ተጫራቾች ፖስታ ጨምሮ በእለቱ ይከፈታል፡፡
8. አሸናፊው ድርጅት አሸናፊነቱ በተገለፀለት ከ7ተከታታይ የስራ ቀናት በኂላ በግንባር ቀርቦ አሸናፊ የሆነበትን ጠቅላላ ዋጋ 10% የውል ማስከበሪያ በማስያዝ በ8 ቀናት ውስጥ ውል መያዝ ይኖርበታል፡፡

**የበለጠ መረጃ ለማግኘት በስልክ ቁጥር** 058 771 66 91/058/178 00 37/ **ደውለው መጠየቅ ይችላሉ፡፡**

- ❖ **የጨረታ መክፈቻ ቀኑ የበአል ቀናት ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን የሚከፈት ይሆናል፡፡**

*ዩኒቨርሲቲው ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው*

***ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ***

Debre Markos University Procurement Administration Process No 1